## የመግለጫዉ ርዕስ

ጻድቅ ብእሲ ዘይትዌከል በፈጣሪሁ፤ በፈጠረው የሚያምን የሚታመን ታላቅ ጻድቅ ሰው አባታችን አባ ተክለሃይማኖት ነው ዕንባ፤ ም.2፡4

ታላቁ ኢትዮጵያዊ ጻድቅ ሐዋርያ አባታችን አባ ተክለ ሃይማኖት በአምላክ ፍቃድ በመልአኩ ብሥራት ከካህኑ ፀጋ ዘአብና ከእናታቸው ከቅድስት እግዚእ ሐርያ ከክርስቶስ ልደት በኋላ በ1192 ዓ.ም. ታህሣሥ 24 ቀን ተወለዱ ካህኑ ፀጋ ዘአብና እግዚእ ሐርያ ሁለቱም በሕጋዊ ጋብቻ የታወቁ በእግዚአብሔር ፊት የጸደቁ ጻድቃን ነበሩ፡፡ አባታችን አባ ተክለ ሃይማኖት በሆድ ሳልሰራህ ሳልፈጥርህ አዉቄህለሁ ከማህፀንም ሳትወጣ ቀድሼሐለሁ በማለት እግዘአብሔር ለነቢዩ ኤርሚያስ ያዘጋጀውን የመመረጥ ዕድል ታላኩን ፀጋ የተቀበሉ ስለመሆናቸው የተጻፈላቸው የሃይማኖት የገድል የትሩፍት ታሪካቸው ምስክር ነው፡፡

ማወቅ መቀደስ ማለት ለተከበረዉ ለተወደደው ነገር አስቀድሞ በልዩ እውቀት በልዩ መንፈስ በእግዚያብሔር ፈቃድ ማዘጋጀት ማለት ነው፡፡ አባታችን አባ ተክለ ሃይማኖት በተወለዱ በሶስተኛ ቀን አሐዱ አብ ቅዱስ አሐዱ ወልድ ቅዱስ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ ብለዉ የሥላሴን ስም ጠርተዉ ማመስገናቸዉ ለቅዱስነት ለሐዋርያነት የእግዚአብሔርን ስም ይዘው በጠነከረ ሃይማኖት በገድል በትሩፋት ለመሞት የመመረጣቸውን ታሪክ የሚያመለክተው የመጀመሪያው ታላቁ ክፍል ነው፡፡ አባታችን አባ ተክለ ሃይማኖት በተወለዱ በሶስተኛ ቀናቸው የሥላሴን ስም ጠርተው ለይተው በማመስገናቸው ልጄ ይህንን የመሰለውን ቃል መናገር የአባትህ ሥራ ነው እስከ ማለት ያደረሳት እናታቸውን እግዚእ ሐርያ እጅግ  ያስደነቃት የምስጋና ቃል ነበር፡፡

አባታችን አባ ተክለ ሃይማኖት የመጀመሪያው ስማቸውን ፍሥሐ ጽዮን የሚለውን ስማቸውን ተለውጦ ተክለ ሃይማኖት እንዲባሉ የነገራቸው ሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል ነው፡፡ ሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል ከእግዚአብሔር በታዘዘዉ መሠረት ስምህ ፍሥሐ ጽዮን አይሁን ተክለ ሃይማኖት ይሁን እንጂ ትርጓሜውም ተክለ አብ፤ ተክለ ወልድ፤ ተክለ መንፈስ ቅዱስ፤ ማለት ስለመሆኑ ተርጉሞላቸዋል፡፡ ይህንኑ የሶስትነት ስሙን ከሰጣቸው በኋላ እግዚአብሔር ራሱ ተገልጦ የዓለም መድኀኒት የመሆን እኔ እየሱስ ክርስቶስ ነኝ በእናትህ ማህፀን ሳለህ ፈጥሬ ያከበርሁህ እኔ ነኝ የእኔ እድል ፋንታ ያደረግሁህ እኔ ነኝ፤ በተወለድህ በሶስተኛ ቀን አሐዱ አብ ቅዱስ፤ አሐዱ ወልድ ቅዱስ፤ አሐዱ ዉእቱ መንፈስ ቅዱስ፤ ብለህ ታመሰግነኝ ዘንድ፤ የምስጋና ሀብት ያሳደርኩብህ እኔ ነኝ የሚለውን የአምላካቸውን ድምፅ የሰሙት አባ ተክለ ሃይማኖት ማዕረግ ቅስናን ከሊቀ ጳጳሱ ከአባ ጌርሎስ ከተቀበሉ በኋላ ነው፡፡

እንግዲህ እግዚአብሔር በፍቃዱ በአምላካዊ ሥልጣኑ መርጦ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሃይማኖት መሳሪያ አድርጎ የሰጠንን ታላቅ ጻድቅ ኢትዮጵያዊ ሐዋርያ አባታችንን አባ ተክለ ሃይማኖትን ስማቸውን ብቻ ሳይሆን ማወቅ የሚገባን ጌታችን በወንጌል እንዳስተማረው እንዳዘዘው፤ የፈጸሙትን ፍጹም የሆነ ገድላቸውን ጠንካራ ሃይማኖታቸውን በመንፈስ ቅዱስ ኀይል የተሰጣቸውን በሽተኞችን የመፈወስ ሙታንን የማስነሳት ሥልጣናቸውን ሁሉ ከመጽሐፈ ገድላቸዉ እንደተጻፈው ልንማረው ልናስተውለው ይገባል፡፡ እሱ እግዚአብሔር በአምላካዊ ቃሉ ያከበራቸዉን ኃይል ተአምር የሰራባቸዉን እንደ ገድላቸው መጠን እንደ ሃይማኖታቸው መጠንከር፤  ሥልጣን የሰጣቸዉን ቅዱሳን፤ ሳንንቅ ሳናቃልል በወንጌል እንደተጻፈው የሰሩትን ገድል ሃይማኖት ትሩፋት በመጽሐፍ ቅዱስ በተገናዘበ ምስጢር ማስተዋል ይገባናል፡፡  በእኔ ከሚያምኑት ከእነዚህ ከተናናሾቹ አንዱን ያሰናከለ የወፍጮ መጅ በአንገቱ ላይ አሥሮ ወደ ጥልቅ ባሕር ቢያስጥሙት ይሻለዋል፤ የሚለዉ አምላካዊ መልእክት ቅዱሳን መለእክትን ጻድቃን ሰማዕታትን ሐዋርያትን ነቢያትን ለሚያቃልሉ ለሚያጥላሉ ደካማ አስተሳሰብ ላላቸዉ ወገኖች የንሰሐ መልእክት ነው፤ የአባቴን ፊት ዘወትር ያያሉ ሁልጊዜም ይቀርባሉ ማለትም ዘወትር በባለሟልነት

በእግዚአብሔር ፊት እንደሚቀርቡ እነግራችኋለዉ ስለዚህ እንዳያስፈርዱባችሁ ተጠንቀቁ ማለቱ ነው ማቲ.18.ቁ1-6 ጌታችን በእኔ የማይሰናከል ንዑድ ክቡር ነው ብሏል ማቲ.11 ቁ. 6 በእኔ የማይሰናከል የማይጠራጠር፤ ክቡር ነው ማለቱ በአስተማረው በሚያስተምረው የወንጌል መልእክት የማይጠራጠር ወደፊትም እሱ በፈቀደው ጊዜ ለወንጌል ትምህርቱ ለሃይማኖቱ ለገድል ለትሩፋቱ የሚያዘጋጃቸውን ቅዱሳን ወዳጆቹን ሁሉ ማሰናከል ስለሆነ የእሱን ቃል የእሱን መልእክተኞች ከማሰናከል እንዲቆጠቡ ነው፡፡ ጌታቸን ያስተማረው ያስተላለፈዉ የወንጌል መልእክት እሱ በመረጣቸዉ ወዳጆቹ እስከ ምጽአት መነገሩን ሲተላለፍ መኖሩን ማስተዋል ይገባናል፡፡ እግዚአብሔር ከፈቀደ ከእናቱ ማህፀን ጀምሮ ቢመርጠው በሕፃንነቱ ቢያዘጋጀዉ በተወለደ በሶስተኛዉ ቀን ፈጣሪውን ቢያመሰግነው ሥልጣኑ ፍቃዱ የእግዚአብሔር ብቻ መሆኑን የማናምን ሰዎች በተለይም በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሥርዓት ያለን ክርስቲያኖች ይህንን የመሰለውን በቅዱሳን ላይ ያለውን ጥርጥር ሰንካላ እምነታችንን ዛሬውን ማስተካከል ማቃናት ይገባናል፡፡

መመረጥ እግዚአብሔር ያነጋገረው ጻድቅ ሲባል ምናልባት እንደ ስምንተኛው ሺህ መነኮሳት የቲሌቢዥን ቤት፣ የመኝታ ቤት፣ የመታጠቢያ ቤት፣ ሳሎን በማማረጥ፣ ከሶፋ ሶፋ በመገለባበጥ፣ ከመኪና መኪና በመለዋወጥ፣ የነበሩትን ዛሬም ያሉትን አለማውያን መነኮሳት አይደለም፡፡ ቅዱሳን ጻድቃን የሚባሉት ከሐዋርያት ጀምሮ አባታችንን አባ ተክለሃይማኖትን የመሳሰሉትን የዕለት ራት የጣት ቀለበት ጫማ በትና ስንቅ የሌላቸዉ መኖሪያ ቤታቸውም ዳዋ ጥሰዉ ደባ ለብሰዉ ድንጋይ ተንተርሰው ጢዛ ልሰው ቅጠል በጥሰዉ ግርማ ሌሊቱን ድምፀ አራዊቱን ፀብአ አጋንንቱን ታግሰው የመከራ ሥጋ ጽዋቸውን እየጠጡ የሞቱን መስቀል ተሸክመው በገድል በሃይማኖት ሙሉ ዘመናቸውን የፈጸሙ ናቸው የእግዚአብሔር ቅዱሳን የሚባሉት፡፡ ከሥጋዊ ከደማዊ ከመንፈሳዊ ጠላት መከላከያ ኃይላቸው የእግዚአብሔር ስም የተጻፈበት ትእምርተ መስቀሉ ነው የመንፈስ ቅዱስ ሰይፍ የሚለው ይሕውም የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነበር፡፡ እነኤርምያስ እነ ቅዱስ ጳዉሎስ እነ ዮሐንስ መጥምቅ ሲመረጡ ገና በናታቸው ማህፀን ነበር አባታችንም አባ ተክለሃይማኖትም እንደነዚህ ቅዱሳን መመረጣቸውን የተጻፈላቸው የገድል የሃይማኖት የትሩፋት ቅዱሰ ታሪካቸው ያስረዳል ገላ.ም.1.ቁ15-17. ሉቃ.1.ቁ13-18 ኢር.ም 1.ቁ7-11 እግዚአብሔር እንዲህ አለኝ ወደምሰድህ ወደ ምልክህ ሁሉ ትሔዳለህና የማዝህንም ሁሉ ትናገራለህና ብላቴና ነኝ አትበል አድንህ ዘንድ ከአንተ ጋር ነኝና፣ ከፊታቸው አትፍራ ይላል፣ እግዚአብሔርም እጁን ዘርግቶ አፌን ዳሰሰ እግዚአብሔርም እነሆ ቃሌን በአፍህ ውስጥ አኖራለሁ እነሆ ትነቅልና ታፈርስ ዘንድ ታጠፋና ትገለብጥ ዘንድ ትሰራና ትተክል ዝንድ በአሕዛብና በመንግሥታት ላይ ዛሬ አድርጌሐለሁ ሹሜሐለሁ ይላል. ኢር.1.ቀ 7-11 ቤተ ጣኦትን ማፍረስ ማጥፋት ከአምልከቱ መንቀል ቤተ እግዚአብሔርን መትከል መተካት ማስተማር ማፅናት የተፈቀደላቸው በእግዚአብሔር ስልጣን የተመረጡ የተጠሩ የተላኩ የተሾሙ ነቢያት ሐዋርያት ካህናት ጻድቃን ሰማዕታት ናቸው፡፡ ቃሉን እንደ ሰማነው እግዚአብሔር ከፈቀደ እግዚአብሔር ከወደደ እግዚአብሔር በቃሉ የመረጣቸውን አባታችንን አባ ተክለ ሃይማኖትንም እግዚአብሔር እጁን ዘርግቶ አፋቸውን ገዳቸዉን ሁለንተና ሰውነታቸውን በመዳሰስ በመንፈስ ቅዱስ ሀብት ሕይወቱን ሊመላባቸዉ አዲስ ኢትዮጵያዊ ሐዋርያ ሊያደርጋቸው እንዳደረጋቸውም ልናውቅ ልናምንም ይገባል፡፡

አባታችን አባ ተክለሃይማኖት በመጽሐፈ ገድላቸው እንደተመዘገበው በታላላቅ የኢትዮጵያ በረሐማ ተራራዎች ላይ የነበሩትን የአጋንንት መስፈሪያዎች የጣኦት ማምለኪያ ዛፎችን ከእግዚአብሔር በተሰጣቸዉ ሥልጣን በሃይማኖት አፍረሰዋል ቆራርጠዋል በፋንታው የኀጢአትን ሥራ ነቅለዉ የጽድቅን ሥራ ተክለዋል በጣኦት በአጋንንት የሚያመልኩትን ወገኖች አስተምረው በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቀው ወደ እውነተኛው አምልኮ እግዚአብሔርን ወደ ማምለክ የመለሱ ታላቅ ኢትዮጵያዊ ሐዋሪያ ናቸው፡፡ እግዚአብሔር እሱ በመረጣቸው በወደዳቸው ቅዱሳን እያደረ እጅግ ብዙ ተአምራታዊ ኀይል ለማድረግ ምንም የሚቸግረው ነገር እንደሌለ በትንቢትም በትርጓሜም ተጽፎአል፡፡ አንበሳውን እባቡን በእግርህ ረግጠህ ትገዛቸዋለህ ተብሎ ለቅዱሳን ጻድቃን

ለሚደረግላቸው ኀይል ተአምር አስቀድሞ ትንቢት መነግሩን በቅን ልቡና ማስተዋል እንችላለን፡፡ እነዚህን የተጠቀሱትን የዱር እንስሳት እንደ በቅሎ እንደ ፈረስ ትገዛቸዋለህ ትቀመጥባቸዋለህ ብሏል፡፡  ደብረ ዳሞ የተባለዉን ታላቁን ገዳም የመሠረቱት የመጀመሪያው ታላቁ ጻድቅ አባ አርጋዊ (ዘሚካኤል) ታላቁን ገደላማ ተራራ የወጡበት የዘንዶውን ሰውነት ይዘው ጨብጠው ከእግዚአብሔር በተፈቀደላቸው ሥልጣን አዝዘዉ እንደነበር በገድላቸዉ እንደተጻፈው ቃሉን ልናስታውስ ይገባል፡፡

እስመ ብየ ተወከለ እድህኖ ይላል ትልቁ ቃል ኪዳን እምነት በእግዚአብሔር ረዳትነት በስሙ ማመን በመሆኑ በእኔ አምኗልና አድነዋለሁ የእኔን ስም ይዟልና በስሜ ማመንን ስሜን መጥራት ወዷልና ከመከራው እሰውረዋለሁ ይለምነኛል እኔም ልመናውን እሰማዋለሁ እቀበለዋለሁ፡፡ ከዚህ ቀደም ከእሱ ጋር ነበርሁ ከእንግዲህ ወዲህም በዘመኑ ሁሉ በመከራው ጊዜ ሁሉ ከእሱ ጋራ እኖራለሁ ከመከራው አድነዋለሁ ከመከራው አድኜ አከብረዋለሁ እሱን አድኜ እመሰገንበታለሁ ክብሬን እገልጥበታለሁ ረጅም ወራት ሰፊ ዘመናት ሰጥቼ ደስ አሰኘዋለሁ ይላል፡፡ ደስታው ጸድቆ በዚህ ዓለመ በተቀበለው መከራ ሥጋ በኋላ በእግዚአብሔር መንግሥት የሚሰጠውን ደስታ ነው፡፡ ይህንን የመሰለው አምላካዊ ቃል እስከ መጨረሻ ሕይወቱ የበለጠ ኀይል ተአምር እንዲያደርግ እንዲሰራ እጠብቀዋለሁ የሚለው ቃል አባታችንን አባ ተክለ ሃይማኖትን ለመሳሰሉ ቅዱሳን ጻድቃን ሰማዕታት ከእግዚአብሔር የተላለፈ ቃል እውነተኛ ቃል ኪዳን መሐላ መሆኑን ልናስተውለው ይገባል መዝ.90.ቁ13-16 ት/ኢሳ 38፡5-7 አመልካች ጥቅሱን ማገናዘብ እንችላለን፡፡

ቅዱሳን ሐዋርያት ጻድቃን ሰማዕታት ቢያከብሯቸዉ ያከብራሉ ቢወዷቸው ይወዳሉ ከእግዚአብሔር በተሰጣቸዉ ቃል ኪዳን ያማልዳሉ በችግሩ በመከራው ጊዜ ሁሉ ይጠብቃሉ በረድኤት በበረከት ያጠግባሉ ቢንቋቸው ቢያቃልሏቸዉው ግን በሌጌዎን ይጥላሉ በነፍስ ይሰቅላሉ፤ ሌጌዎን የተባለው ለቅጣት ለማጥፋት የተዘጋጀ የታዘዘ መልአክ ነው እንጂ አጋንንት መናፍሳት ርኩሳን እንዳይመስሉን፡፡ አባታችን አባ ተክለ ሃይማኖት በተወለዱ በ16 አመት ዕድሜያቸው ከአባታቸው ከፀጋዘአብ ጋር የድቁና ክህነት ተቀብለው ከአማራው ሃገር ወደሃገራቸው ሸዋ ሲመለሱ ብዙ መንገድ ተጉዘው ስንቅ አልቆባቸው የሚያሳድራቸው አጥተው እስቲ ደግ ሰው እንዳለ የፈጣሪያችን ፍቅር ይደርበት እንደሌለም ሰላምታዬ ወደኔ ይመለስ በማለት እንደ ጌታችን ቃል ተናግረው  ማቴ.10.13 ሰላምታዉን በሰማ ጊዜ ተቆጥቶ እናትህን ፍቅር ይስጣት ከእኔ ዘንድ ልታድር መጣህን ብሎ ከዚያው ከቤቱ ከተቀመጡት አንዱ ተነሥቶ አባ ተክለ ሃይይማኖትን መታቸው አባ ተክለ ሃይማኖትም በጣም አለቀሱ ወዲያው የመታቸውን ሰውየ ሰላምታ ብሰጥህ እንደ መቀበል ግፍ ትመልስልኛለህ ግፍ ትሰጠኛለህ ብለው የእግዚአብሔር ባለሟል ሚካኤል ይህንን ሰው በእኔ ላይ ያደረገውን ግፍ ሁሉ አታይምን፤ የእግዚአብሔር ባለሟል አንተ ሚካኤል የረዳትነትህን ኀይል አሳየኝ በማለት አባ ተክለ ሃይማኖት ሲጸልዩ፤ አባ ተክለሃይማኖትን የደበደባቸውን ባለጌ የሀገሩ ሰዎች ሁሉ እያዩ ወደ ሰማይ ወጥቶ ተዘቅዝቆ ተሰቅሎ ከዚያው ከአየር ላይ እንዳለ ብዙ ሲገረፍ ሲመታ የሚገርፈው የሚመታው ግን አይታይም፤ ድምፅም እንደ ጥቅል ነፋስ ሲጮህ ይሰማል ከዚያዉ ከአየር ላይ እንዳለ፤ እናንት የእግዚአብሔር ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ብላችሁ ይቅር በሉኝ እያለ ሲጮኽ ይሰማል፡፡ የሀገሩ ሰዎችም ይህንን አይተው ሰምተው በመደንገጥ እኛም ባለማወቅ ቸል ብለናልና እኛንም ይቅር በሉን እያሉ የተክለ ሃይማኖትን አባት ፅጋ ዘአብንና አባ ተክለ ሃይማኖትን ለመኗቸው ስለዚህ እየደጋገሙ ይቅር በሉን እያሉ ማለዷቸዉ ይላል፡፡ በአየር የተሰቀለው ሰውየ አንተ ብላቴና እባክህ ይቅር በለኝ እያለ በተለይ አባ ተክለ ሃይማኖትን ሲለምን የሰማ ነበር አካልህ ትንሽ ቢመስልም ሥራህ ግን ከሰማያት ይበልጣል እኔ ባለማወቄ የትዕቢት ሥራ ሠርቻለሁ በእኔ ላይ ኀይልህን ገለጥህ እንግዲህ ዳግመኛ እንደዚህ ያሉ ሥራ አልሰራምና ይቅር በለኝ በማለቱ ብዙ ጮኸ፡፡  አባ ተክለ ሃይማኖትም በአየር ላይ የተሰቀለውን ሰውዬ ኀጢአቱን እንዳመነ ስለተገነዘቡ እግዚአብሔርን ስለ በደሉ ሰዎች የሚፈርደውን ፍርድ ፈጥኖ እንደሚበቀልላቸው አወቅህን ሲሉት አወን አወቅሁ በማለቱ የሰቀለህ አምላክ ያውርድህ

አሉትና የተሰቀለው ሰውየ ከምድር እስኪ.ወርድ ጥቂት ጥቂ.ት እያለ ወደታች ወረደ በጀርባው ላይ በእሳት እንደተቃጠለ ሆኖ የግርፋት ምልክት ታይቷል፡፡

እንግዲህ ታሪኩን ብቻ ሳይሆን ተአምራቱን እናስተውል ይህንን የመሰለ ተአምር የገለጠ እግዚእብሔር ከነቢያት ከሐዋርያት ጀመሮ ለአባ ተክለ ሃይማኖት የሰጣቸውን ሥልጣን መንፈሳዊ ኀይል ተአምር ለመግለጥ ነው፡፡ ገድለ ተክለሃይማኖትም 20፡ ቁ 1-59 ሐዋርያው ታዴዎስ በሚያስተምርበት ሀገር ከአንድ ገበሬ ቤት ተጠግቶ ገበሬው ለሐዋርያው ታዴዎስ ስለ አደረገው እንግዳ የመቀበል ቸርነቱ ሐዋርያው ታዴዎስ ገበሬውን በክርስቶስ አምላክነት ለማሳመን ለማስተማር ብሎ የገበሬውን በሬዎች እንደተጠመዱ ራሱ ሐዋርያው ታዴዮስ እያረሰ ዕለቱን ስንዴ ዘርቶ ለእሸት ለመሰዋዕት በማድረስ ይህንን በሐዋርያው ታዴዎስ ሥልጣን የተፈጸመውን ታላቅ ተአምር የእግዚአብሔር ኀይል የተመለከቱ አረማውያን የሚሰሩት የሚያደርጉት ቢያጡ ሰይጣን እንደመራቸው ሰይጣን እንዳመለከታቸው ሐዋርያው ታዴዮስ በሚወጣበት በሚገባበት መንገድ ፊት ለፊት ዕራቁቷን ሐፍረተ ሥጋዋን የገለጠች ሴት በዝሙት ሥራዋ እንድታሳስትው ለማጥመድ ብለው በሰሩት ተንኮል የሐዋርያውን ምክሩን ትምህርቱን ባለመቀበሏ በነፋስ ኀይል ወደ አየር አሰቅሏት ለተወሰነ ቀን ሰትቀጣ ቆይታ ብዙ አልቅሳ ጩኸት አብዝታ ሰዎች በሰሩት ተንኮል በገንዘብ ኀይል መገፋፋቷንም ስለአመነች ስለተፀፀተች ሐዋርያው ታዴዎስ ከተሰቀለችበት አየር ላይ እንድትወርድ ካደረገ በኋላ አስተምሮ አሳምኖ አጥምቆ የመንግሥተ ሰማያት ባለቤት እንደሆነች በገድለ ሐዋርያትና በስንክሳር መጻሐፋችን ተጽፏል፡፡ እኔ የላክሁትን የተቀበለ እኔን ተቀበለ እኔን በተቀበለ ማለትም እኔ የላክሁትን በተቀበለ እኔ አድርበታለሁ እኔን በተቀበለ አባቴ ያድርበታል በቃል እኔን የተቀበለ አባቴን ተቀበለ እኔ ባደርሁበት አባቴ ያድርበታል ዩሐ.13.ቁ 20 እናንተን የሰማ እኔን ሰማ እናንተን እምቢ ያለ እኔን እምቢ አለ እኔን እምቢ ያለ የላከኝን አባቴን እምቢ ማለቱ ነው እኔን የሰማ የላከኝን አባቴን ሰማ ሉቃ 10-16 እናንተን የተቀበለ እኔን ተቀበለ ማለትም እናንተን በተቀበለ ሰው እኔ አድርበታለሁ እኔን የተቀበለ አባቴን ተቀበለ እኔ ባደርሁበትም አባቴ ያድርበታል ብሏል፤ ነቢዩን በነቢዩ ስም የተቀበለ ነቢዩን ነቢዩነቱን አምኖ የተቀበለ ነቢዩ የሚያገኘውን እኔ የምሰጠውን ዋጋ ያገኛል፡፡

እውነተኛውን ጻድቅ ጻድቅ ብሎ የተቀበለ ጻድቅ የሚያገኘውን እኔ የምሰጠውን ያገኛል ስለ አምላከ ኢሳይያስ ስለ አምላከ ኤርምያስ ብሎ ደሐውን የተቀበለ እኔ የምሰጠውን ነቢይ የሚያገኘውን ዋጋ ያገኛል ዋጋው መድራዊ ሐላፊ ጠፊ ሳይሆን የመንግሥተ ሰማያት የጽድቅ ዋጋ ነው፡፡ ስለ አምላከ እንጦሰ ወመቃርሰ፤ ስለ አምላከ ተክለሃይማኖት፤ ስለ አምላከ ገብረመንፈስ ቅዱስ፤ ብሎ ድሐውን የተቀበለ ጻድቅ የሚያገኝውን እኔ የምሰጠውን ያገኛል፡፡ ስለ አምላከ ጴጥሮስ፤ ስለ አምላከ ጳውሎስ ብሎ በእኔ ካመኑ መዕመናን አንድ ጽዋ ውሃ ያጠጣ ዋጋውን እንደማያጣ በእውነት እነግራችኋለሁ ብሏል ማቴ.10፡40-42 የክርስቶስ ወገን ናችሁና ብሎ ማንም በስሜ ጽዋ ውሃ ያጠጣችሁ ሰማያዊ ዋጋውን አያጣም ብዬ እንደማያጣ በእውነት እነግራችኋለሁ ማር፡ ቁ 9፡40-41 ቃሉን እናስተውል ሁሉም ነገር ጾም ጸሎቱም ምጽዋት ስግደት ቁመቱ በእግዚአብሔር ስም ብቻ መፈፀሙ ቅዱሳን ነቢያት ሐዋርያት ጻድቃን ሰማዕታት በክርስቶስ በስሙ ተጠርተው ስሙን አምልከው ስሙን አስተምረው ለዱር አራዊት ተሰጥተው ወደ ጉድጓድ ወደ እሳት ተጥለው በአረማውያን አደባባይ ታስረው ተገርፈው ቁልቁል ተሰቅለው ቆዳቸውን እንደ ሌጦ ተገፈው እንደ በጎች በሰይፍ ታርደው፤ ደማቸውን አፍሰው ስለክርስቶስ አምላክነት ስለመሰከሩ ስለ ሃይማኖታቸው ጽናት እግዚአብሔር ለስማቸው ለታሪካቸው ለወዳጅነቱ የገባላቸው የሰጣቸው ቃልኪዳን ነው፡፡

የሁሉም ቅዱሳን እግዚእብሔር የገባላቸው ቃል ኪዳን በገድል በድርሳን በየተአምር መጽሐፋቸው ተጽፎላቸዋል 1ኛ.ቆሮ 14. ሐዋሪያው ቅዱስ ጳውሎስ በዕብራውያን መልእክቱ እግዚአብሔር እሱ በመረጣቸው እሱ በጠራቸው ቅዱሳን እያደረ እየተገለጠ የሚያደርገውን የሚመሰክርላቸውን ኀይል እያሳደረላቸው እሱ ሰለወደደ ስለፈቀደ መንፈስ

ቅዱስ እንዳደላቸው መጠን የሚደረግላቸውን ተአምር ቅዱስ ጳዉሎስ እንዳስተማረበት መመልከት ይቻላል ዕብ.2.ቁ 3-5 ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በየመልእክቱ እየጠቀሰ እንዳስተማረበት እግዚአብሔር በየጊዜው ለሚያስነሳቸው የወንጌል መምህራን አባ ተክለሃይማኖትን የመሳሰሉ ቅዱሳን ጻድቃን ሰማዕታት የሚቀበሉትን መከራ ሥጋ የሚሰጣቸውንም ሰማያዊ ዋጋ እያገናዘበ አስተምሮ እንደ ጻፈው ለሕማም ለስደት ለእስራት ለሥጋዊ ሞት ያዘጋጃቸውን እነሱን በሃይማኖት አፀና፣ በሃይማኖት ያፀናቸውን ያበረታቸውን እነሱን በአዲስ ሰማያዊ ልጅነት በመንፈስ ቅዱስ ኀይል አበረታቸው። ስለዚህ ነገር ስለዚህ ምስጢር እንግዲህ ምን እንላለን እግዚአብሔር ከእነዚህ ቅዱሳን ጻድቃን ሰማዕታት ጋር ከሆነ ማን ይችላቸዋል ማን ይችለናል ብለው በሃይማኖት ተነሱ ብሏል። እግዚአብሔርን አምነው ወደው ፈቅደው ለተከተሉት ቅዱሳን ቀርቶ ከእኛ ይልቅ ለልጁስ እንኳ አላዘነለትም ስለሁላችሁ ቤዛ መዳኛ እንዲሆን ለሞት አሳልፎ ሰጠው እንጂ ብሏል መስጠትም መሰጠትም ፈቃድ የሁለቱም ነውና፣ ስለዚህ ሁሉንም የማይሰጠን ምንድነው፣ ምን ነገር አለ?? እግዚአብሔር የመረጣቸውን ሰዎች የሚነቅላቸው ከእግዚአብሔር የሚለያቸው ማን ነው? እሱ ካጸደቀ ማነው የሚኮንን? እያለ ከሙታን ሁሉ አስቀድሞ ተነሥቶ በአምላካዊ ሥልጣኑ ላይ ተቀምጦ የመከራቸውን የሞት የስቃያቸውን ሰማያዊ ዋጋ በእውነተኛ ፍርዱ የሚሰጥ በመሆኑ ከክርስቶስ ፍቅር ከክርስቶስ ሃይማኖት ተነሥተው ኀዘኑን መከራውን ስደቱን መራብ መጠማቱን መራቆትን ጭንቀቱን ሁሉ ታግሠው ለመታረድ ለመቆረጥ እንደ ተዘጋጁ የበዓላት በጎች መሆናቸውን ራሱን ጨምሮ በግልፅ አስተምሮበታል. ሮሜ.8፡30-36 ዘሁልቅ.14፡9. ኢሳ 50፡ቁ .8-10 አሁንም በአንደኛ ቆሮንጦስ መልእክቱ አዋቂዎችህ ነን ጥበበኞች ነን የሚሉትን ያሳፍራቸው ዘንድ እግዚአብሔር የዚህን ዓለም አላዋቂዎች የማያቁትን ያልተማሩትን መረጠ እንጂ፣ ጠቢባን ነን የሰውን አዕምሮ በእውቀታችን በመጽሐፋችን እናንፀዋለን እናስተካክለዋለን የሚሉትን ፈረሳውያን ያሳፍራቸው ዘንድ ዓሣ ወጋሪ ልብደ ሰፊ ቆዳ ሰፊ የነበሩ ሐዋርያትን ቀራጮችን ኀጥአን መፀብሓንን መረጠ እንጂ፣

ከድሃ ከአላዋቂ ቤተሰብ ወገን የነበሩትን ቅዱሳን ስማዕታትን ጻድቃን አባ ተክለ ሃይማኖትን፣ አባ ዮሐኒ አባ ኢየሱስ ምዓ የመሳሰሉትን ኢትዮጵያን ቅዱሳን መረጠ እንጂ፣ ኃይለኞች ነን የሚሉትን ያሳፍራቸው ዘንድ ደካሞችን መረጠ እንጂ ከቁጥር የገቡትን ያሳፍራቸው ዘንድ እግዚአብሔር ከቁጥር ያልገቡትን ተንቀው ተጠልተው ያልተቆጠሩትን ዘመድ አዝማድ የሌላቸውን መረጠ እንጂ ሰው ሁሉ አስቀድሞ በመታወቁ አስቀድሞ በመቆጠሩ እንዳይመካ ብሏል፣ ይህንን በመሰለው ቃል የተጠሩ ቅዱሳን ያገኙት የተጠቀሙበት ነገር ምንድነዉ? ትልቁ ክብራቸዉ መጠራታቸው መመረጣቸው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ፈቃድ ብቻ መሆኑ ነው። ያገኙበትም ጥቅም ሥጋዊ ሹመት ሽልማት ጥበብ ብልጥግና ተድላ ደስታ ሳይሆን ዘለዓለማዊ የሆነ ጽድቅ ንጽሕና ቅድስና ያለበት ሰማያዊ መዳንን ሕይወትን ብቻ ነው። እስከ አሁን የተመለከትነውን የመሰለ የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ከራሱ ከቅዱስ ጳውሎስ በፊት ከተጠሩት ቅዱሳን ጀምሮ ከቅዱስ ጳውሎስ በኋላ ለተጠሩትም አባታችንን አባ ተክለ ሃይማኖትን ለመሳሰሉት ለሃይማኖት ለከባድ ገድል ለተመረጡት ቅዱሳን ከዚያም ከአባ ተክለ ሃይማኖት በኋላ ለነበሩት ወደፊትም እስከ ምፅዓት በክርስቶስ ስም ተጠርተው ስሙን ይዘው ስሙን አምልከው በስሙ መከራ ሥጋ ተቀብለው ወጥተው ወርደው አስተምረው በአረማውያን አደባባይ ታስረው ተገርፈው በሐዋርያነት በሰማዕትነት ሕይወታቸውን ለሚያሳልፉ ቅዱሳን ጻድቃን ሁሉ ቅዱስ ጳውሎስ ያስተማረው በጽሑፍ ያስተላለፈው ትንቢታዊ መልእክት አለው።

በመጋዝ የሰነጠቋቸው እነ ኢሳያስን በድንጋይ የወግሩዋቸው እነ እስጢፋኖስን በሰይፍ መተው የገደሏቸው ራሱን ቅዱስ ጳውሎስን የመሳሰሉትን የገረፉቸው አባ ተክለ ሃይማኖትም ሰለ ክርስቶስ ስም በብዙ አረማውያን መገረፋቸው ተጽፏል የዘበቱባቸው አሥረው ያሰቃዩዋቸው አሉ ነበሩ ብሏል። ማቅና አድፍ የፍየል ሌጦ ቆዳ ለብሰው ገዳማትን የዞሩ አሉ የተቸገሩ የተጨነቁ ነበሩ ይህንን ዓለም አንፈልገውም ብለው መከራውን የተቀበሉ አሉ ዱር ለዱር ተራራ ለተራራ ዋሻ ለዋሻ ፈረፈር ለፈረፈር የዞሩ የተቸገሩ ቸግርን እስከ ሞት የታገሡ ነበሩ በማለት የጻፈው ሀገርን ሕዝብን በጾም በፀሎታቸው ለትሩፋቸዉ

የጠቀሙትን ከእግዚአብሔር ጋር ያስተረቁትን ታላቁን አባታችንን አባ ተክለ ሃይማኖትን የመሳሰሉትን ቅዱሳን አበው የነበሩበትን ዘመነ ሰማዕታትን ዘመነ ጻድቃንን ዘመነ መዕመናንን መንፈሳዊ ገድላቸውን ለመመስከር ለማስተማር ነዉ. ዕብ.11.ቁ 37-40 አባታችን አባ ተክለ ሃይማኖት ከቤተክርስቲያን ታሪክ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ የጠቀስናቸውን የቅዱሳን ሐዋርያትን ሃይማኖት ሥልጣነ ክህነትን ከጌታችን ተቀብለው በጣኦት አምልኮ የተበከሉ ለአጋንንት ለመናፍስት ርኩሳን የተገዙ እነመተሎሜን የመርሰሉ ቀንደኛ አረማውያን ገዥዎችን በማስተማራቸው አባ ተክለ ሃይማኖትንና መስል ካህናትን ምዕመናንን በእርጥብ ቁርበት ከነሕይወታቸው እያስጠቀለለ ከእንጨት ከገመድ በተሰራ ቆፎ ውስጥ እያሳፈነ ከታላቅ ገደል ውስጥ እያስጠላቸው ሁለት ሶስት ጊዜ በእግዚአብሔር ኋይል ከገደሉ የወጡ የጻት ለአረማዊ መተሎሜ የተሰጡ አባ ተክለ ሃይማኖትንና ካህናት መዕመናንም እጅግ ብዙ መሆናቸው ተጽፏል ገድለ ተክ ሃይ፡ ገጽ 121. ምዕራፍ 39 ቁ120-160 መመልከት ይቻላል::

አባታችን አባ ተክለ ሃይማኖት አረማዊ መተሎሜ ወዳለበት ዳሞት ወደ ተባለው የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገረ ሔደው መተሎሜንና ቤተሰቡን መኳንንቱን አስተምረው በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቀዉ ሥጋዉንና ደሙን አቀብለዉ ለአረማዊ መተሎሜ የራሳቸዉን ስም ፍሥሐ ጽዮን ብለዉ ሰይመዉ በዳሞት ብቻ ከ12 ዓመት በላይ በማስተማራቸዉ ታሪኩ እጅግ በጣም ሰፋ ባለ ሁኔታ ተጽፏል፤ መንክር እግዚአብሔር በላዕለ ቅዱሳኒሁ፤ እግዚአብሔር በወዳጆቹ ቅዱሳን አድሮ የሚሠራዉ ድንቅ ሥራ አባ ተክለ ሃይማኖትን በመሳሰሉ ጻድቃን የሚያደርገዉ ትምህርት ተአምራቱ እጅግ ዕፁብ ድንቅ ነዉ:: አምላከ እስራኤል ውእቱ ይሁብ ኋይለ ወጽንአ ለሕዝቡ መዝ 67.ቁ35 የእስራኤል ፈጣሪ እሱ እግዚአብሔር ለወገኖቹ ለመረጣቸዉ ወዳጆቹ ኀይል እየሰጠ የሚያበረታ ነው ብሏል እሱ ከመረጣቸዉ ለነቢይነት ለሐዋርያነት ለሰማዕትነት በጾም በጸሎቱ በትሩፋቱ ሕዝቡን አሕዛቡን የሚጠቅም ቅዱሱን ጻድቁን ሰዉ እያስነሳ በመንፈስ ቅዱስ እየቀሰቀሰ እየመረጠ ያዘጋጅ እንደነበር የብሉይ ኪዳን ታሪክ ትልቁ ምስክር ነዉ:: ይትባረክ እግዚእብሔር እንዳለዉ ነቢዩ ይህንን የመሰለ የቅዱሳንን መመረጥ የፈቀደ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን:: አባታችንን አባ ተክለሃይማኖትን ላስነሳ ለመረጠ ለቀደሰ እግዚእብሔር ለኢትዮጵያ ታላቅ አባት ታላቅ ሐዋርያ አድርጎ ለሾመ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ዛሬም ነገም ለወደፊትም እስከ ምፅአት ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን::

አባታችን አባ ተክለ ሃይማኖት ከብዙ አዕላፈ አዕለፍት ሕዝብ መካከል የተመረጡ ቅዱስ አባት ክቡር ጻድቅ መባላቸዉ እጅግ የሚያስመካ ነዉ እንጂ የሚያሳፍር የሚያጠራጥር አይደለም:: አንድ ታሪክ በበጎነቱም በክፉነቱም ይጻፋል ለሕዝቡ ለአሕዛቡ ይነገራል ይተላለፋል ይተረካልም ታሪክ ተብሏልና ደግሞም ታሪክ በበጎነቱም ሆነ በክፉነቱ የሃይማኖት መግለጫ መታወቂያ ነዉ፤ የአባታችን አባ ተክለ ሃይማኖት ታሪክ ግን ገና በማህፀን የተመሠረተ በመሆኑ በቅዱስነት በንጹሕ ጻድቅነት እየለመለመ እጅግ ድንቅ የሆነ የመንግሥተ ሰማያት ፍሬ ክብር እያፈራ የመጣ ነዉ፤ አባ ተክለ ሃይማኖት በአረማዊ ንጉሥ መተሎሜ ዘመን ከካህናቱ ጋር ከቤተ ክርስቲያን የተማረከዉ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የተቀረፀ ታቦት በአብርሃ ወአጽብሐ ዘመነ መንግሥት በነበረዉ ጳጳስ በአባ ከሳቴ ብርሃን እጅ የተባረከ ታቦት የሚል ጽሑፍ ያለበት ከመተሎሜ አልጋዉ ትራስ ዉስጥ በተገኘ ጊዜ አባታችን አባ ተክለ ሃይማኖት በረከሱት አሕዛብ ቤት ስለ ነበረዉ ስለተገኘዉ ታቦት ምን ማድረግ ይሻለኛል በማለት እጅግ በተሰበረ መንፈስ እያዘኑ እያለቀሱ ቅዱስ ንጹሕ ሥጋህንና ክቡር ደምህን በምን እሠራለሁ መሰዋዕት ቁርባን ያለ ታቦት አይሰራምና ወይስ በጳጳሱ እጅ የተባረከዉን ታቦት እኔ ዳግመኛ መባረክ ይሆንልኛል፤ ይገባኛል፤ ይቻለኛል፤ እያሉ አባ ተክለ ሃይማኖት ንጹሕ በሆነ ፍቅር ትሕትና ወደ እግዚእብሔር እያዘኑ ሲያቀርቡ ከልብ ሲቆርቆሩ የሰማቸዉ ያዳመጣቸው እግዚአብሔር ወዳጄ ተክለ ሃይማኖት ታቦትን ልታከብር ካህናቱንና ዲያቆናትን ልትሾም ጣኦታቱን ልትሽር ልታጠፋ እኔ ልኬሐለሁና አትዘን፤ አሁንም ታቦቱን አክብረዉ መባረኩንም አትፍራ በዚች በጨለማይቱ ሀገር በዳሞት እንደኔ የዓለም ብርሃን አድርጌሐለሁና ሹመትህም ሊቃነ ጳጳሳት እንደ ሾሚቸዉ እንደ ሌሎቹ

ጳጳሳት አይደለም ላንተ ግን እኔ ፍጹም ሥልጣን ሰጥቼ በአንደበቴ ሾሜሐለሁ የሚለዉ የእግዚአብሔር ፈቃድ የመጣላቸዉ ታቦቱንም መባረክ የተፈቀደላቸዉ አባታችን አባ ተክለ ሃይማኖት ናቸዉ፡፡ ሌላዉንም ንዋየ ቅድሳት ለማግኘት በተጨነቁ ጊዜ ማግኘት ባልቻሉበት ጊዜ ቅብዓ ሜሮኑን መጸሐፈ ቅዳሴዉን አምጥቶ የሰጣቸዉን እንዳዘዝሁህ አድርግ ብሎሐል ብሎ የእግዚአብሔርን መልእክት ሁል ጊዜ እየተገለጠ የሚነግራቸዉ ሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል ነበር ገድለ.ተ. ሃይ .ገጽ.129 ምዕ 39.ቁ 145-154 መመልከት ይቻላል፡፡

ወደ ወንጌል መልእክት ስንመለከት ጌታችን እናንተ የዓለም ብርሃን ናቸሁ እናንተ በተራራ ላይ የተሰራ መንደር በተራራ ላይ የታነፀ ከተማ ናችሁ በቤት ዉስጥ ላሉት ሁሉ እንዲያበራ እንዲያሳይ በመቅረዝ ላይ የተተከለ መብራት ናችሁ በማለት ጌታችን በምሳሌ ያስተላለፈዉ የወንጌሉ ቃል በመጀመሪያዉ መቶ ዘመን ለነበሩ በሐዋርያት ዘመን ብቻ ያበቃ መልእክት አልነበረም፡፡ ባለመሆኑም አባታችን አባ ተክለ ሃይማኖት ከ99 ዓመት ዕድሜያቸዉ መካከል ከአርባ ከአምሳ በላይ የሚሆነዉን ከሕፃንነት ዕድሜያቸዉ ጀምሮ በሚሠሩት በሚያደርጉት ተአምራት በኢትዮጵያ ግዛት ሁሉ እዉነተኛዉ የወንጌል ትምህርት ብርሃን ሆነዉ አብርተዋል በተራራ ላይ የተሰራ መንደር ከተማ ለማንም ለሁሉም እንደሚታይ የአባ ተክለ ሃይማኖትም መግባር ትሩፍታቸዉ ጠንክረዉ የሃይማኖት ግድላቸዉ በኢትዮጵያ ተራራዎች ላይ ብቻ ሣይሆን ከኢትዮጵያ ዉጭ ወጣ ብሎ ባለዉ ሀገር በግብፅ በኢየሩሳሌም በተሰሩ ታላላቅ ገዳማት በታወቁ የሃይማኖት አባቶች ዘንድ የአባ ተክለ ሃይማኖት ገድል ሃይማኖታችዉ የታወቀ የተደነቀላቸዉ እጅግ የበቁ ታላቅ ጻድቅነታቸዉ በመጽሐፈ ገድላቸዉ በስፋት ተጽፏል. ገጽ166-168 ም. 48.ቁ 1-12 መመልከት እንችላለን፡፡ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዕንቅብ ሊደፋበት ወይም በአልጋ ስር መብራት ለማኖር ማንም ሰዉ መብራት አያበራም በቤት ዉስጥ ላለዉ ሁሉ እንዲያበራ እንዲያሳይ ከፍ ካለዉ ቦታ ላይ መቆም አለበት እንጂ እንዳለዉ አባታችን አባ ተክለ ሃይማኖት ከእግዚአብሔር በተሰጣቸዉ ታላላቅ ተአምራትን የማድረግ የመሥራት የሞተን በማዳን የታመመዉን በሽተኛ በክርስቶስ ስም በመፈወስ በአጋንንት ቁራኛ የተያዘዉን በማስለቀቅ የጣኦታትን ቤት በእግዚአብሔር ስም በሃይማኖት በማፈራረስ የሃይማኖት የወንጌል ትምህርት መብራት፣ መብራቱን ለሁሉም ኢትዮጵያዊ ወገኖች ቤተሰቦች ሁሉ አብርተዉላቸዋል፡፡

አባታችን አባ ተክለ ሃይማኖት አማራ ሳይንት ዳዳ ከተባለዉ ታላቅ ተራራ ላይ ቀድም ብሎ ጉዲት የምትባለዉ ሟርተኛ ፈላሻ ታመልከዉ የነበረዉ በኋላም ሕዝቡ አሕዛቡ ሁሉ በዘመኑ የነበረዉ የሳይንቱ ንጉሥ ሳይቀር የሚያመልከዉ በ170 ክንድ ርዝመት የሚለካዉን ዘንዶ አባ ተክለ ሃይማኖት የገደሉት በጉልበት በሥጋዊ ጥበብ ልዩ መሳሪያ ሳይሆን አርእየነ ደጋሁ ከተባለዉ ደቀ መዝሙራቸዉ ጋር ከተራራዉ ላይ ለጾም ለጸሎት ልዩ ለሆነ ተባሕትዋ በወጡበት ጊዜ ሰዉ መብላት የለመደዉ ዘንዶ የሚበላ አገኘሁ ብሎ መላሱን ሲመዝባቸዉ አባ ተክለ ሃይማኖት በተሰጣቸዉ ዕባቡን ጌንጡን የመግዛት የማዘዝ ሥልጣን መንፈሳዊ ተአምር በመስቀል ምልክት ባማተቡበት ጊዜ ከሁለት እንደ ጨርቅ ተሰንጥቆ ከገደሉ ከየድንጋዩ ላይ ተንጥልጥሎ የምድር የደን አራዊት የሰማይ አሞሮች እንኳ እንዳይበሉት ጠልተዉት ገምቶ ተበላሽቶ እንደነበር ሰፋ ብሎ የተጻፈዉ የገድል መጽሐፋቸዉ ያስረዳል፡፡ ይህንን ታላቅ ታሪክ ሃይማኖታዊ ተአምር የተመለከተዉ በዘንዶዉ ያመልክ ዘንዶዉን እጅግ ይፈራዉ ያከብረዉ የነበረዉ የሳይንቱን ንጉሥና እጅግ ብዛት ያለዉን ሕዝብ አባታችን አባ ተክለ ሃይማኖት በእግዚአብሔር አምላክነት እንዲያምን አስተምረው በዚያው ሀገር ዙሐ በተባለዉ ታላቁ ወንዝ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እንዳጠመቁዋቸዉ ተጽፏል፡፡ በዚያዉ ዘንዶዉ ይመለክበት በነበረዉ ተራራ ላይ በታቦተ አርባዕቱ እንስሳት ስም ቤተክርስቲያን እንደሰሩላቸዉ በመጽሐፈ ገድላቸዉ ተጽፏል ም.50 ቁ 1-10 አባታችን አባ ተክለ ሃይማኖት በጣኦት አምልኮ በታወቁት በኢትዮጵያ ተራራማ ቦታዎች ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል እየታዘዙ የጣኦት አምልኮ በተሰፋፋባቸዉ ለታላላቅ ዛፎች በሚሰገድበት የአጋንንት መስዋዕት በሚሰዋበት ሁሉ ጌታችን እንዳዘዛቸዉ አባታችን አባ ተክለ ሃይማኖት በተራራ ላይ የተሰራች መንደር በተራራ ላይ የተከተመ የወንጌል

መምህር ከተማ መሆናቸዉን አንዳንድ ሰዎች ቢክዱ ለመሰወር ለመጠራጠር ቢሞክሩ የአባ ተከለ ሃይማኖት ጠንካራ ሃይማኖታቸዉ ታሪካዊ ገድላቸዉ ሊሰዉረዉ ሊክደዉ አይችልም፡፡

ንጹሕ ቅዱስ ትሩፋታቸዉ በደም የተጻፈዉ ገድላቸዉ በእግዚአብሔር ፊት ያቀረበዉን በእግዚአብሔር መዝገብ የተጻፈዉን ፍጡር ሊለዉጠዉ ሊገለብጠዉ አይችልም፡፡ ገድል ተአምር ደርሳን ከቅዱሳን መጻህፍት ቃል አንደኛዉ የሃይማኖት መታወቂያ መግለጫ ስለመሆኑ ጠለቅ ብለን አስተዉለን ከሊቃዉንት ጠይቀን ልንረዳ ይገባል፡፡ አባታችን አባ ተክለሃይማኖት ኢየሱስ ክርስቶስ ማንም ሰዉ መብራት አብርቶ መብራት ማብራቱ ዕንቅብ ወይም ቅርጫት ሊደፉበት ወይም በአልጋ ሥር ሊኖረዉ አይደለም በቤት ዉስጥ ላለዉ ሁሉ እንዲያበራ እንጂ በማለት ያስተላለፈዉን አምላካዊ መልእክት የተከተሉ ታላቅ ሐዋርያ በመሆናቸዉ፤ የጣኦት አምልኮ በገነነባቸው በአጋንንት መናፍስት ርኩሳን በታሰሩባቸዉ ኢትዮጵያዉያን ወገኖች ሁሉ የወንጌል ትምህርት መብራት የዘረጉ በመላዉ ኢትዮጵያ የጣኦት አምልኮ ፊት ያበሩ ያቀጣጠሉ ታላቁ ኢትዮጵያዊ ሐዋርያ ስለመሆናቸዉ የመሰከረላቸዉ አምላካቸዉ ኢየሱስ ክርስቶስ ነዉ አመልካች ጥቅስ ማቲ.5፡14-17 ማር.16፡16-19 የቅዱሳን የጻድቃን ዋናዉ መሠረቱ በመጀመርያ በወንጌል እንደተጻፈ ለሐዋርያት በሔዳችሁ ለማስተማር በወጣችሁ ጊዜ መንግሥተ ሰማያት ልትሰጥ ቀርባለችና ንስሐ ግቡ እያላችሁ ወንጌል በእግዚአብሔር ስም ስበኩ አስተምሩ ድዉያንን በሽተኞችን ፈዉሱ ለምጻሞችን አንፁ አጋንንትን አስወጡ ሙታንን አንሡ በከንቱ የወሰዳችሁትን በከንቱ ስጡ ዋጋ ሳትቀበሉ የተማራችሁን የወንጌል ቃል ዋጋ ሳትቀበሉ አስተምሩ፡፡ ወርቅ ብር ሳንቲም በመቀነታችሁ አትያዙ ለመንገድም የስንቅ ከረጢት አትያዙ በሚለዉ ክርስቶስ በሰጣቸዉ ሥልጣን ፈቃደኛ የሆነዉን ሕዝብ በወንጌል ትምህርት ማሰባሰብ ማዘጋጀት ፈቃደኛ ያልሆነዉን አዉግዞ ለመለየት፤ ከየሰዉ ላይ የተቆረኙትን አጋንንት በተሰጣቸዉ ሥልጣን እንዲወጡ ማዘዝ ማዉገዝ እንደሚችሉ የተሰጣቸዉ ታላቅ ሥልጣን ነዉ፤ ያመኑትን ግን ይህች ተአምራት ትከተላቸዋለች በስሜም ሰይጣናትን ያወጣሉ በሌላም አዲስ ቋንቋ ይናገራሉ ማለትም ኃይል ተአምር ማድረጉ እስከ ምጽዓት በሚነሱት ሐዋርያት ጻድቃንን ሰማዕታት ሳይለያቸዉ ሲከተላቸዉ ይኖራል ማለት ነዉ፡፡

በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ማመን በስሙ መጠራት ስሙን ማመልክ ስሙን ይዘዉ በአረማዉያን አደባባይ ስለ ክርስቶስ ስም ለመሞት ማስተማር መመስከር ነዉ፤ እባቦችን ይይዛሉ የሚገድልም መርዝ ቢጠጡ አይጎዳቸዉ ማለቱ እባብ ማለት ሰይጣን ነዉ መርዝ ማለት ሰይጣን መልካም ሥራ አስመስሎ ክፉ ሥራዉ ክፉ ማሰራቱ ጣኦት ማስመለኩ ለአጋንንት ለዛፍ ለቃልቻ እንዲሰግዱ እንዲገዙ ማድረጉ ነዉ፤ መርዝ መጠጣት ማለትም የሰይጣንንና የፈቃደ ሥጋዉን የክፉ ሥራ ምኞት ጠሩን ፈተናዉን በጾም በጸሎት በፍቅር በትዕግሥት ድል ማድረግ ነዉ፤ እጃቸዉንም ድዉያውያን ላይ ያሳርፋሉ ድዉያውያንም ይድናሉ ብሏል እጅ በመጫን በቃል በመናገር ብቻ ሳይሆን ቅዱስን ጻድቃን ሰማዕታት በጥላቸዉ በሰዉነታቸዉ ጥላ በልብሳቸዉ በመቋሚያቸዉ በመነሳንሳቸዉ ማዳናቸዉ መፈወሳቸዉ በማያጥራጥር ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፏል ማር.16፡16. ማቲ.10፡ 6-10 እባብን መያዝ ማለትም አንገቱን ጅራቱን መያዝ መጨበጥ ብቻ ሳይሆን ጌታችን በሰጣቸዉ ሥልጣን መሠረት የሰይጣንን የክፉ ሥራ የሐሰት ሥራ መርዙን ሰዉ መያዙን መቆራኘቱን ድል አድርጎ ማዘዝ መለየት ብቻ ነዉ፡፡ እስከ አሁን ከወንጌል እንደጠቀስነዉ በሽተኛዉን መፈወስ የሞተዉን ማስነሳት ጋኔኑን አጋንንቱን ከየአለበት ከሰዉም ላይ ሰዉን ለማሳሳት በተሰባሰበበት ታላላቅ ዛፍ ታላላቅ ተራራ ላይ ለማሰወጣት ለማባረርም ለአባታችን ለአባ ተክለ ሃይማኖት ከእግዚአብሔር የተሰጣቸዉ ሥልጣን ነበራቸዉ በዚሁ መሠረት በመጽሐፈ ገድላቸዉ እጅግ ሰፋ ባለ ትርጓሜ እንደተጻፈዉ ማስተዋል አንብቦ መረዳት ይቻላል፡፡ አባታችን አባ ተክለ ሃይማኖት ከጠንካራዉ ሃይማኖታቸዉ ከታላላቅ ገድል ብዙዉ ትሩፋታቸዉ ሌላዉ እጅግ የሚደነቅላቸዉ ጌታችን እንዳስተማረዉ እንዳስጠነቀቀዉ በሰዉ ፊት አባ አባ መባልን፤ በውዳሴ ከንቱ መመስገንን መከበርን እጅግ አጥብቀዉ መጥላታቸዉ ማዉገዛቸዉ ከከንቱ ምድራዊ ምስጋና መሸሻቸዉ የሚደነቅላቸዉ ታሪክ ነዉ፡፡

ጌታችን ባነጋገራቸዉ በተለያየ ጊዜ መንፈሳዊ ፀጋዉን አምላካዊ ጥበቃዉን በጨመረላቸዉ ጊዜ ሁሉ እኔን ኃጢአተኛዉን ለእኔ ለኃጥኡ ይኸ ክብር የሚገባኝ አይደለም በማለት ራሳቸዉን በጣም ዝቅ እያደረጉ ለትሕትና ለጉስቁልና የሰጡ ስለመሆናቸዉ በመጽሐፈ ገድላቸዉ በስፋት ተጽፏል፡፡ ጌታችን ልዩ በሆነ ምሳሌ መስሎ ወንጌልን ባስተማረበት ምሳሌዉ የመጀመሪያዎቹ ሐዋርያት አባቶች በዉዳሴ ከንቱ ብቻ ተጠልፈዉ ዋናዉን ሰማያዊ ዋጋቸዉን እንዳያጡ በሰይጣን ወጥመድ ዉስጥ እንዳይገቡ በሐላፊዉ ምድራዊ ምስጋና ብቻ እንዳይወድቁ፤ ከእናንተ የሚያርስ ገበሬ ወይም ከብት የሚጠብቅ ሎሌ ያለዉ ሀብታም ባለቤት ቢኖር ሎሌዉ ከእርሻዉ ሲመለስ ፈጥነህ እጅህን ታጠብና ለእራት ተቀመጥ ከእኔ ጋራ ብላ ይለዋልን አይለዉም፤ ነገር ግን እኔ የምበላዉን እራቴን አዘጋጅልኝ እስክበላ እስክጠጣ ድረስ ወገብህን ታጥቀህ ወይም መብራት ይዘህ አገልግለኝ ከዚያ በኋላ አንተ ትበላለህ ትጠጣለህም የሚለዉ አይደለምን? ያም ሎሌ ጌታዉ ያዘዘዉን ስለአደረገ ስለሥራ በዉኑ ይመሰገናልን? የታዘዘዉን መሥራት የሚገባዉን ደመወዝ የሚበላበትን የተቀጠረበትን ሥርቷል እንጂ በሚለዉ አምላካዊ ቃል ብቻ የሚመሩ ታላቅ ጻድቅ ናቸዉ፤ እንዲሁም እናንተ የታዘዛችሁትን ሁሉ አድርጋችሁ ሥርታችሁ በዉዳሴ ከንቱ ሳትጠለፉ እኛስ ሰነፎች ሎሌዎች ነን በሉ ልናደርገዉ ልንሠራዉ የሚገባንን አደረግን ሥራን በሉ እንጂ፤ ደግሞም አጋንንት ስለ ተገዙላቸዉ ደስ አይበላችሁ ደስ ሊላችሁ የሚገባዉ ስማችሁ በመንግሥተ ሰማያት መዝገብ ስለ ተጻፈ ነዉ እንጂ በማለት አባ ተክለ ሃይማኖትም ጌታችን በወንጌለ ቃሉ ያስተላለፈዉን ማስጠንቀቂያ ተከትለዉ የሚያስተምሩ ገድል ትሩፋት የሚሰሩ በሃይማኖት እጅግ የጠነከሩ ሐዋርያ ስለ መሆናቸዉ መጽሐፈ ገድላቸዉን ተመልክቶ ከወንጌሉ ቃል ጋር አገናዝቦ ከመረዳት የበለጠ ታላቅ ጸጋ ሊኖር አይችልም አመልካች ጥቅሱን ሉቃ. 17፡1-11 መመልከት ይቻላል፡፡ አባታችን አባ ተክለ ሃይማኖት ስለ ጠቅላላዉ የእግዚአብሔር አገልጋይነታቸዉን የሚመሰክር ከፈጣሪያቸዉ ሰባት አክሊላት ተቀብለዋል፡፡

በመጀመሪያ ጌታ ተገልጦ ወዳጄ ተክለ ሃይማኖት ሆይ በሰዉ እጅ የማይላከዉን ይህንን የመንግሥት አዳራሽ ዉሰድ አላቸዉ የመለኮትን ነገር የሚናገር የእሳት አንደበት ያለዉ የመንግሥት ልብስ አለበሳቸዉ ይላል፡፡ ከዚያ በኋላ በመስቀል ምልክት የተጌጡትን ሰባቱን የብርሃን አክሊላት አቀዳጃቸዉ

1. ስለ ቀናች ሃይማኖትህ ብሎ
2. ሃይማኖትን ለማስተማር መላዋን ኢትዮጵያን ስለ መዞርህ ብሎ
3. ከአረማዉያን ሕዝብ ጋር በሃይማኖት ስትታገል ደምህን ስለማፍሰስህ ብሎ
4. ወደ ኢየሩሳሌም ወርደህ ልዩ ልዩ የቅዱሳንን ቦታዎችን ስለመሳለምህ
5. ጣኦታትንና አጋንንትን ስለማጥፋትህ ብሎ
6. በሰባት አመታት ቁመት የአንዱ እግርህ አገዳ በመሰበሩ ብሎ
7. ስለ ብዙዉ ጾም ጸሎትህ ስግደትህ ስለ ልብስህ ንጽሕና ቅድስና ብሎ

እነዚህን በቁጥር ሰባት የሆኑትን የብርሃን አክሊላትን ከሰጣቸዉ በኋላ በገነት በመንግሥተ ሰማያት የተሾመ የተሸለመ መሆኑን የገለጠባት የጌታችን እጅግ ሰፊ የሆነዉ ቃሉ በገድለ መጽሐፋቸዉ ተጽፏል ም. 58፡1-19 አባታችን አባ ተክለ ሃይማኖት እንዴት በምን ምክንያት ስድስት ክንፍ ሊሰጣቸዉ ቻለ? ለሙቀት ወይም ለድምቀት የተሰጣቸዉ ሳይሆን እጅግ የሚወዳቸዉ እግዚአብሔር አምላካዊ ተዓምራቱን ሊገልጥባቸዉ ሊያስተምርባቸዉ ስለ ፈቀደ ብቻ ነዉ፡፡ ታላቁን ገዳም ደብረ ዳሞን ለመሳለም መዉጫ መዉረጃዉ በሰዉ እጅ የተሰራ ገመድ ስለመሆኑ ዛሬም ታሪኩ ይነገራል ሁሉም ምዕመናን ያዉቁታል፡፡ አባ ተክለ ሃይማኖት በደብረ ዳሞ ብቻ የገዳሙን ማህበር መነኮሳትን በማገልገል 12 ዓመታት ቆይተዉ ከእግዚአብሔር መልአክ እንደ ታዘዙ ሌሎችን የትግራይን ገዳማት በመሳለም በየገዳማቱ የሚኖሩትን ቅዱሳን አበው ለመገናኘት ለመተዋወቅ ሲሔዱ የደብረ ዳሞዉ አባ ምኔት አባ ዮሐኒ፤ አባ ተክለ ሃይማኖትን ለመሸኘት የገዳሙን መነኮሳት አስከትለዉ ከላይ ወደታች እስከ ዋናዉ በር አድርሰዋቸዉ ሸኝተዋቸዉ ሲመለሱ ያለ ጠንካራ ገመድ መዉረድ መዉጣት የማይቻለዉ

አርባ ክንድ ያህል ርዝመት ካለዉ ገደል ላይ አባታችን አባ ተክለ ሃይማኖት እንደ ተለመደዉ ወገባቸዉን በገመዱ ታስረዉ መዉረድ ሲጀምሩ የገዳሙ አባ ምኒት አባ ዮሐኒ መነኮሳቱ ሁሉ ከላይ ከመዉረጃዉ በላይ ሆነዉ እየተመለከቱዋቸዉ ሳለ ወዲያዉ ብዙ ሳይቆይ አባ ተክለ ሃይማኖት የሚወርዱበት ገመዱ ከላይ ከተተከለበት ከካስማዉ ሥር ሲበጠስ ለአባታችን ለአባ ተክለ ሃይማኖት ስድስት ክንፍ ከእግዚአብሔር ስለተሰጣቸዉ በዚያ ታላቅ ጸጋ ክንፎቻቸዉን እየመቱ ሲበሩ አባ ምኒቱ አባ ዮሐኒና የገዳሙ መነኮሳት እየተመለከቷቸዉ፤ ገዳሙን ደብረ ዳሙን ሶስት ጊዜ ዞረዉ ሔደዋል የሚል ቀደም ብሎ የተጻፈ ታሪክ ተመልክተናል፡፡ በመጽሐፈ ገድላቸዉ እንደተጻፈዉም ሶስት ዝንግ ወርዉሮ የሚያርፍበትን ያህል በክንፋቸዉ ሲበሩ ታይተዋል ይላል ከላይ ወደታች የሚወረድበት ገመድ ለማንም ተበጥሶ አያዉቅም ነገር ግን እግዚአብሔር በአባ ተክለ ሃይማኖት ላይ የነበረዉን የማይወሰን ፍቅሩን ተአምራቱን ለመግለጥ ስለ ፈቀደ ብቻ ነዉ፡፡ ያንን ለአባ ተክለ ሃይማኖት የተደረገላቸዉን የእግዚአብሔር ተአምር የተመለከቱ የደብረ ዳሞ መነኮሳት መንክር እግዚአብሔር በላዕለ ቅዱሳኒሁ መዝ.6፡ 7-35 እግዚአብሔር ራሱ በመረጣቸዉ በወደዳቸዉ ቅዱሳኑ አድሮ የሚሠራዉ እጅግ ድንቅ ሥራ ነዉ እያሉ በማድነቅ ለአባ ተክለ ሃይማኖት ይህንን ተአምር ያደረገላቸዉን እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ወደ ገዳማቸዉ ተመለሱ ይላል ገድለ ተክ.ሃይ. 47፡12-15 አባታችን የተሰጣቸውን ክንፍ ስድስት ስለመሆኑ የሱራፌል ክንፍ ስድስት ስለሆነ፤ እግዚ.አብሔርም እንደ ካህናተ ሰማይ ሱራፌል፤ አባ ተክል ሃይማኖትን ያከበረበት ቃል ስልሰጣቸው ነው፡፡ ኢሳ. 6፡2-4

እግዚአብሔር አባ ተክለ ሃይማኖትን ለመሳሰሉት እሱ ለመረጣቸዉ ቅዱሳን ወዳጆቹ የተለየ ተአምር ኳይል ብርታትን እንደሚሰጥ አስቀድሞ ትንቢት መነገሩም ተጽፏል ጎበዛዝቱም ፈጽሞ ይወድቃሉ እግዚአብሔርን በመተማመን የሚጠባበቁ ግን ኃይላቸዉን ያድሳሉ እንደ ንስር እንደ አሞራ በክንፍ ይወጣሉ (ይሮጣሉ) አይታክቱም አይደክሙም ይሄዳሉ ብኋል ት.ኢሳ. 40፡ 29-31 እግዚአብሔርን በመተማመን እግዚአብሔርን በማምለክ በየተራራዉ ላይ የቆመዉን የጣኦት አምልኮ በማፍረስ በታላላቅ ዛፎች ላይ የሰፈረዉን የአጋንንት መንጋ በእግዚአብሔር ሥልጣን በመደምሰስ ወደ እዉነተኛ አምላክ ወደ እግዚአብሔር አምልኮ በመመለስ ደማቸዉን በማፍሰስ ሥጋቸዉን በመበጣጠስ የታወቁ መልካም ሃይማኖታቸዉ በገድል በተሩፍታቸዉ የጻደቁ አንደኛዉ ታላቁ ጻድቅ አባታችን አባ ተክለ ሃይማኖት ስለ መሆናቸዉ ምንም አያጠራጥርም ይህንንም የመሰለዉን ነቢዩ በትንቢቱ እንደተናገረዉ እንደጠቀስነዉ አምላካዊ መልእክት ቅዱሳን ሁሉ ለሚያደርጉት የሃይማኖታቸዉ ብቃት ብርታት መንፈሳዊ ትሩፋት መንፈሳዊ ጉልበት እንደሚጨመርላቸዉ መረዳት መገንዘብ ይቻላል፡፡ አሜን፡፡